# ውድድር የሌለበት ምርጫ
# በሕዝብ ማላገጫ፤
### ወለላው አንድነት

የግንቦትን ወር ፳፻፪ ዓ. ም. ምርጫ አስመልክቶ ኢሕአዴግ መቶ በመቶ ማሸነፉን የዋልታ ጋዜጣ ድል አበሠረ። አንባቢዎቻችን፤ በዚህ ምሽት የዕለቱ የምርጫ ሂደት እንደሚከተለው እንዘግባለን።

| | |
|---|---|
| መንግሥት | - ኢሕአዴግ |
| አወዳዳሪ | - ኢሕአዴግ |
| ገንዘብ አዳይ | - ኢሕአዴግ |
| አስመራጭ | - ኢሕአዴግ |
| የምርጫ ቦርድ | - ኢሕአዴግ |
| ዳኛ | - ኢሕአዴግ |
| ፖሊስ | - ኢሕአዴግ |
| አሳሪ | - ኢሕአዴግ |
| ታዛቢ | - ኢሕአዴግ |
| ተወዳዳሪ | - ኢሕአዴግ |
| ገንዘብ ተቀባይ | - ኢሕአዴግ |
| የምርጫ ሳጥን ቆላፊ | - ኢሕአዴግ |
| የምርጫ ሳጥን ተሸካሚ | - የኢሕአዴግ ቅጥረኞች |
| አሸናፊ | - ኢሕአዴግ |
| አጨብጫቢ | - ኢሕአዴግን የተጠጉ አለቅላቂዎች |

ዛሬ በከፍተኛ ውድድር ያገኙትን አናፊነት አስመልክቶ፤ ይኼንን ድል ከግቡ ለማድረስ ከፍተኛ ተጋድሎ ያደረጉት፣ ሁልጊዜም አሸናፊ፣ እና ታታሪው የተከበሩት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በረከት ስምዖን፤

> “በአፍሪካ ውስጥ ታይቶ የማይታወቅ ድል ስለሆነ፤ የማስታወቂያ ሚኒስትር ሠራተኞች በሙሉ ከዛሬ ጀምራችሁ ኢሕአዴግን ሕዝቡ እንዲያመልክ ሌት ከቀን ተግታችሁ መሥራት አለባችሁ።”

ብለዋቸዋል።

የሙያ ባልደረባቸው አለቅየው ጠቅላይ ሚስትር መለሰ ዜናዊ በበኩላቸው፤ ይኼንኑ ድል አስመልክቶ ሲናገሩ፤

> “ከዚህ ድላችን ምዕራባዊያን ሊማሩበት ይገባል፤ ያደረግነው ውድድር ተፎካካሪ የሌለውና ዴሞክራሲን የሚያስተምር ነው።”

ብለዋል።
በመቀጠልም፤

> “በሀገራችን፤ በመብራት ቢፈለግ ተወዳዳሪ የሌለው አኩሪ ምርጫ ነው።”

ሲሉ የምርጫ ሳጥኑን በተሸካሚነት ያገለገሉት፤ አቶ ልደቱ አያሌው በማጨብጨብ ተናግረዋል። ጥሩ አፍ አላቸው። ጥሩ አጨብጫቢም መሆናቸውን ሕዝብ መስክሮላቸዋል።

የዕለት ጉርሱን ለማግኘት ደፋ ቀና ባዩ ሕዝብ፤ ከኢሕአዴግ ሌላ፤ ፍላጎቱን እና መብቱን አስከብሮ የሀገሩን አንድነት የሚጠብቅለት አማራጭ በምርጫው በማጣቱ፤ “ቀን እስኪያልፍ ያለፋል” ብሏል። ምርጫቸውን ከጠሰጡ በኋላ ከበሩ ለጠበቃቸው የዋልታ ጋዜጠኛ ላቀረበላቸው የአስተያየት ጥያቄ፤

“እንዲህም ያለ ውድድር ታይቶም ተሰቶም አይታወቅ። ተወዳዳሪም አገይገኝበት።”

ብለዋል። ጋዜጠኛው አከታትሎ፣

“የኢሕአዴግ ጠላቶች፣ ኢአዴሕዴግ ለራሱ እንዲመቸው፣ ሆን ብሎ አመራረጡን ምስቅልቅል አደረገው፣ በማለት ስም ያጠፋሉ። በዚህ ላይ እርስዎ ምን ይላሉ?”

በማለት ላቀረበላቸው ጥያቄ፣

“የት አሉና። እዚህ ያለነው እኛ። ምርጫው ቀላል ነበር። ምንም የሚያደናግር ነገር የለበትም። ካርድ መቀበል። ፊት ለፊቱ ካለው ሳጥን መክተት። ይህ ምን ችግር አለበት! ስም አጥፊ በላቸው።”

በማለት መልሰዋል።

ነገ በጣም ቁጥሩ የበዛ ሕዝብ የሚወጣበት ሰላማዊ ሰልፍ እንዲደረግ ጥብቅ ትዕዛዝ ከጠቅላይ ሚኒስትሩ መተለፉን የአጋዚ ተዋጊ ጦር ዋና አዛዥ ግልፅ አድርገዋል። በዚህ ሰልፍ የሚነገቡት ፅሑፎችና የሚደጋገሙት መፈክሮች ቀደም ሲል ተዘጋጅተው፣ በየቀበሌው መከፋፈላቸው ግልፅ ሆኗል። ሃሞት ያለው ባለመኖሩ፣ *<u>እንዴት ከምርጫው በፊት ይኼ ሁሉ ተጠናቀቀ?</u>* ብሎ የጠየቀ የለም።

ለዚህ ሰላማዊ ሰልፍ ይረዳ ዘንድ፣ እያንዳንዱ የኢሕአዴግ አባል የጎረቤቱን ስም ዝርዝር በኪሱ እንዲይዝ የእሕአዴግ የፖለቲካ ኃላፊ በጥብቅ አስገንዝበዋል። እንደሳቸው አባባል፣

“ኢሕአዴግ የሕዝቦች ፓርቲ ስለሆነ፣ እያንዳንዱን የብሔር አባል ማጥናትና፣ የያንዳንዱን የብሔር አባል የጥቅም ጎን ከጎረቤቱ ያለው የእሕአዴግ አባል ማወቁ አስፈላጊ ነው።”

በማለት በአቸናፊነት ኩራት ፎክረዋል። ሃተታቸውን በመቀጠልም፣

“በዕውነቱ ከሆነ፣ የሕዝቦች የፖለቲካ ተሳትፎ ከግል ጥቅማቸው ጋር የተሣሠረ መሆኑን፣ ኢሕአዴግ ለዓለም እያስተማረ ነው። በዚህ እንኮራበታለን። መሬት በጃችን ነው። ማዳበሪያ በጃችንነው። የቀበሌው ቤት በጃችን ነው። ሥራ በሙሉ በጃችን ነው። ለየሱቁ ፈቃድ መሥጠትና የፍጆታ ዕቃዎችን ማከፋፈል በጃችን ነው። ለሕዝቦች ተቆርቋሪ እኛ ብቻ ስለሆን ሀገሪቱ በጃችን ናት። እጅግ ከፍተኛ ሊቅና በዓለም ተወዳዳሪ የማገኝላቸው መሪያችን፣ ጠቅላይ ሚንስትር መለሰ ዜናዊ፣ ‘እያንዳንዱን ተቃዋሚ የምናንበረክከው ከውድድር ውጭ በማድረግ ነው፣’ ባሉት መሠረት፣ ተወዳዳሪ በፍፁም እንዳይገኝ የተቻለውን ሁሉ አድርገናል።”

ብለዋል። ከጎናቸው የነበሩት የሠፈሩ ካድሬ፣

“ለዚህ ይረዳ ዘንድ በየመንደሩ ያለነው ምልምል ካድሬዎች እያንዳንዱ የብሔር ሕዝቦች አባል የፖለቲካ ተሳትፎውንና አመራረጡን ከበላይ አካል በተላለፈልን መሠረት እናውቃለን።”

በማለት አብሥረዋል።